AABE
Accounting and Auditing Board of Ethiopia
የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ

ከኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

ኢኮኖሚ

# ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ለውጥን የተመለከተ የአፈፃፀም መመሪያ

የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 መሠረት የተቋቋመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፡፡ ቦርዱ የተቋቋመበት ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ የተሟላ፣ ግልጽ እና በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡ በተጨማሪም ያልተማከለ የነበረውን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ በማማከል ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ለማጎልበት፤ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ምሶሶዎች ለመደገፍ፣ የፋይናንስ ቀውስ እና የድርጅቶችን ውድቀት ስጋት እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን አሉታዊ የኢኮኖሚ ውጤቶች ለመቀነስ ከድርጅቶች የሚገኘውን የፋይናንስ መረጃ አቅርቦት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎችን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

ይህንን ዓላማ ለማሳካት ያስችል ዘንድ ሪፖርት አቅራቢ አካላት(በሕግ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ የተጣለባቸው አካላት) የሂሳብ መግለጫቸውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች (International Financial Reporting Standards-IFRS) መሠረት ማዘጋጀት እና ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 8 ላይ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ቦርዱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሪፖርት አቅራቢ አካላትን የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ብሎ በመለየት የፋይናንስ ሪፖርታቸውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች መሠረት አዘጋጅተው ለቦርዱ ማቅረብ የሚጠበቅባቸውን ጊዜ "ፍኖተ-ካርታ (Road-Map)" አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በፍኖተ-ካርታው(Road-Map) መሠረት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት በ2015 ዓ.ም በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች(International Financial Reporting Standards, IFRS) መሠረት፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች በ2016 ዓ.ም ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች በተዘጋጀው የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች(International Financial Reporting Standards for Small and Medium Enterprises, IFRS for SME) መሠረት እንዲሁም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት በ2016 ዓ.ም በዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች (International Public Sector Accounting Standards, IPSAS) መሠረት የሂሳብ መግለጫቸውን አዘጋጅተው ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

በዚህ መሠረት 1005 ድርጅቶች ፉል IFRS ተግብረው ፋይናንሻል ስቴትመንታቸውን ወደ ለቦርዱ አቅርበዋል፡፡ IFRS for SMEs ስታንዳርድን ተግብረው ወደ ቦርዱ ያመጡ 129 ድርጅቶች ያሉ ሲሆን IPSAS ተግብረው ወደ ቦርዱ ያመጡት ደግሞ 313 ናቸው፡፡ በአጠቃላይ አንድ ሺህ 447 የሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶች ቦርዱ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ቀርቧል፡፡

በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች (International Financial Reporting Standards-IFRS) መሠረት ሪፖርት አቅራቢ አካላት ያላቸውን ቋሚ ንብረት እና ሌሎች ሀብቶች ዋጋ እንዲሁም ያለባቸውን ዕዳ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ አኳያ እንደገና በማስተመን የሚገኘውን ውጤት(ትርፍ ወይም ኪሳራ) በሂሳብ መግለጫቸው

**በሕግ የፋይናንስ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ የተጣለባቸው አካላት የሂሳብ መግለጫቸውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች (International Financial Reporting Standards-IFRS) መሠረት ማዘጋጀት እና ለቦርዱ ማቅረብ እንዳለባቸው በአዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 8 ላይ ተደንግጓል**

የሀብት እና ዕዳ መግለጫ ላይ የተጠራቀመ/ያልተከፋፈለ ትርፍ አካውንት (Retained Earning Account) ወይም ሌላ ማንኛውም አግባብነት ያለው አካውንት(If appropriate any other Account) ውስጥ እንዲያሳዩ ይገደዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሚደረገው የሀብት እና ዕዳ ትመና የሚከሰት ትርፍና ኪሳራን ዕጣ ፈንታ ወይም አጠቃቀም(ለምን ዓላማ ሊውል እንደሚችል) በደረጃዎቹ ላይ በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡

ስለሆነም ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ለውጥ አመዘጋገብ፣ አጠቃቀም እና ተያያዥ ጉዳዮች በተመለከተ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ወጥነት ያለው እና የሕዝብ ጥቅምን ያማከለ አሠራር እንዲከተሉ ማድረግ የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 4(2)(ሀ) እና አንቀጽ 53(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት "የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች አተገባበርን ተከትሎ ከሚደረግ የሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ለውጥ አፈፃፀም መመሪያ" አዘጋጅቷል፡፡ ይሄውም መመሪያ ቁጥር 985/2016 የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች አተገባበርን ተከትሎ ከሚደረግ የሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ለውጥ አፈፃፀም መመሪያ ነው፡፡

**በዚህ መመሪያ መሠረት የሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ፤**

ሪፖርት አቅራቢ አካላት ከነባሩ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት ወደ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች ሽግግር ሲያደርጉ ወይም ከሽግግር በኋላ በሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ፖሊሲ ወይም ደረጃዎቹ በሚፈቅዱት አኳኋን በየጊዜው ወቅታዊ የገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ የሚፈፀም የሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ ነው፡፡

**ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ጭማሪ፤**

ሪፖርት አቅራቢ አካላት ከነባሩ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት ወደ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች ሽግግር ሲያደርጉ ከሚያደርጉት የሀብት ትመና ወይም ወደኋላ በመሄድ ከሚያደርጉት ማስተካከያ፤ ወይም ከሽግግር በኋላ በሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ፖሊሲ ወይም ደረጃዎቹ በሚፈቅዱት አኳኋን በየጊዜው ወቅታዊ የገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ ከሚያደርጉት የሀብት ትመና የሚገኝ የሀብት ጭማሪ ነው፡፡

**ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ቅናሽ፤**

ሪፖርት አቅራቢ አካላት ከነባሩ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሥርዓት ወደ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎች ሽግግር ሲያደርጉ ከሚያደርጉት የሀብት ትመና ወይም ወደኋላ በመሄድ ከሚያደርጉት ማስተካከያ፤ ወይም ከሽግግር በኋላ በሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ፖሊሲ ወይም ደረጃዎቹ በሚፈቅዱት አኳኋን በየጊዜው ወቅታዊ የገበያ ዋጋን መሠረት በማድረግ ከሚያደርጉት የሀብት ትመና የሚገኝ የሀብት ቅናሽ ነው፡፡

በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 2 ሥር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋሙ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ ማናቸውም ሪፖርት አቅራቢ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ለውጥን አስመልክቶ መመሪያው ምን ይላል?**

**ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ጭማሪ**

1. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኘውን ጭማሪ ወደ ጥሬ ገንዘብ ያልተቀየረ እና የማይመነዘር ትርፍ በመሆኑ ለዋና ገንዘብ ማሳደጊያነት ወይም ለትርፍ ድርሻ ክፍፍል ማዋል አይችልም፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) መሠረት ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኘውን ጭማሪ የተጣራ ሀብት ርዕስ ሥር "የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃ ትግበራ ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የተገኘ መጠባበቂያ" በሚል ከሌላ ሊከፋፈል ከሚችል የተጣራ ሀብት ተለይቶ መመዝገብ አለበት፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) እና (2) ቢኖርም የእርጅና እና የጉዳት ቅናሽ በሚደረግበት ሀብት ላይ በሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ ምክንያት የተገኘው ጭማሪ የእርጅና እና የጉዳት ቅናሽ ከግብር በኋላ ተሰልቶ በየዓመቱ ለዋና ገንዘብ ማሳደጊያ ወይም ለትርፍ ድርሻ ክፍፍል ሊውል ይችላል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) እና (2) ቢኖርም የእርጅና ቅናሽ የማይደረግበት ሀብት ላይ በሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ ምክንያት የተገኘው ጭማሪ ንብረቱ ላይ ጉዳት ሲደርስበት፣ ሲሸጥ ወይም አገልግሎት መስጠት አቁሞ ሲወገድ ብቻ ወደ ያልተከፋፈለ ትርፍ በማዞር ለዋና ገንዘብ ማሳደጊያ ወይም ለትርፍ ድርሻ ክፍፍል ታሳቢ ሊሆን ይችላል፡፡፡

5. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች ከተገበረ በኋላ በተከታታይ ዓመታት በሚያደርገው የሀብት ትመና የሚገኝ ጭማሪ ወደ ጥሬ ገንዘብ ያልተቀየረ እና የማይመነዘር ትርፍ በመሆኑ ለዋና ገንዘብ ማሳደጊያነት ወይም ለትርፍ ድርሻ ክፍፍል ማዋል አይችልም፡፡

**ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ቅናሽ፡-**

ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎችን ሲተገብር ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚያገኘው መጠን ከነባሩ የመዝገብ ዋጋ ቀንሶ ከተገኘ ልዩነቱ ካልተከፋፈለ ትርፍ ቋት ላይ ተቀናሽ መደረግ አለበት፡፡

**መመሪያው ስለተጨማሪ ዕዳ የሚከተለውን ያትታል፡-**

የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲተገበር እንደ ሠራተኛ የሥራ ስንብት እና የሠራተኛ ዓመታዊ ዕረፍት ዕዳ ያለ ቀድሞ ያልተመዘገበ ዕዳ ወይም ቀድሞ ተመዝግቦ ማስተካከያ ተደርጎለት መጠኑ ከነባር የመዝገብ ዋጋ የሚበልጥ ከሆነ ልዩነቱ ካልተከፋፈለ ትርፍ ቋት ላይ ተቀናሽ መደረግ አለበት፡፡

**ስለሚቻቻሉ ሀብት እና ዕዳዎች፡-**

የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች ሲተገበር በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃ 16 መሠረት በአንድ በኩል በሀብት የመጠቀም መብት በሌላ በኩል ደግሞ የሊዝ ዕዳ ካጋጠመ የሊዝ ዕዳው ከመጠቀም መብት ተቀናሽ ተደርጎ የሚተርፍ ካለ ክፍፍል በማይደረግበት ቋት ማለትም "በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃ ትግበራ ከሀብት ትመና የተገኘ መጠባበቂያ" ርዕስ ውስጥ ይመዘገባል፡፡

**ስለሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች፡-**

ሪፖርት አቅራቢው አካል የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅት ከሆነ ከሀብት ትመና ወይም ማስተካከያ የሚገኝ ጭማሪ ለአስተዳደር ሥራዎች ወጪ እና ለድርጅቱ የፕሮጀክት ሥራ ክፍያ ማዋል እንዲሁም ለሌላ አካል በስጦታ ማስተላለፍ አይችልም፡፡

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ መመሪያው በፍትሕ ሚኒስቴር የተመዘገበ የሀገሪቱ የሕግ አካል ሆኖ በመጽናት በኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ድረ-ገጽ ላይ ተጭኖ ይገኛል፡፡